# የሲሳይ መንግስቴ አዲሱ  ቅንጭብ ትንተና ወደ ተሳሳተ ማደማደሚያ!!

በቀለሙ    በለጠ- ባህር ዳር

10-05-17

‘’ ጥቂቶች ቀራጦች ያልተንበረከክነው፤

ነገ ዕልፍ እንሆናለን ታሪክ ምስክር ነው’’ ፡፡

የኢህዴን/ብአዴን የትግል ታሪክ ማጠንጠኛ ስንኞች ናቸው፡፡ የባለታሪኩ ድርጅት መስራችና  የግጥሙ ደራሲ ህላዌ ዮሴፍ፤  ለዘመናት ተንሰራፍቶ የነበረው ግፈኛ ስርዓት ለማስወገድ  በኢትዮጲያ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝብቦች መብትና እኩልነት  ላይ ያደርስ የነበረውን አሉታዊ ተፅዕኖ ለማስወገድ ከአፍላ ወጣትነት ዕድሜው ጀምሮ ህይወቱን በሙሉ አሳልፎ የሰጠ ታጋይ ነው፡፡  ህላዌ ትግሉ የወሰደውን ረጅም ገዜና እየጠየቀውን ዕልህ አስጨራሽ የአካልና ህይወት መስዋዕትነት ፅናትና ፈተና እንዲሁ በዝርው አላለፈውም፡፡ ይልቁንም በስነ-ፁሁፍ ምሁራን ዘንድ ዘመን ተሻጋሪና አይረሴነት አለው ተብሎ በሚታመንበት የኪነጥበብ -ስራ (በስነ-ግጥም) እንካችሁ ብሎናል፡፡

ስነ-ግጥሙ ብአዴን ያለፈበትን ውጣ ውረድ  ስኬትና ውድቀት ፤ተስፋና  የቀጣይ ዘመናት  አቅጣጫን በር አንኳኩቶ ይተነብያል፡፡ በአዋቂ ኩሉ ደራሲ አቅምና ችሎታ፡፡ የአታጋይ ድርጅቱ (ኢህዴን /ብአዴን) የቆመለት ህዝባዊ አላማና ፅናት በርካታ አብዮታዊ ታጋዮች የአካልና ህይወት መስዋዕትነት ከፍለውበታል፡፡ በርካቶችም ተሸንፈው ከትግሉ ገሸሽ ብለዋል ፡፡  እንደ ሲሳይ መንግስቴ አዲሱ አይነቶች ደግሞ  ከአረንቋው ዘቅተዋል፡፡

የአማራ ብሄራዊ ክልል በዋነኛነት የአማራ ህዝብ መገኛ ነው፡፡ የአገው፤ ቅማንት፤ ህምራ፤ የኦሮሞና አርጎባ ህዝቦችም በብሄራዊ ክልሉ በሰላምና በፍቅር ይኖራሉ፡፡  ከክልሉ ውጭ ቁጥራቸው በርከት ያሉ የአማራ

ተወላጆች በሌሎች ክልሎች እንደሚኖሩት ሁሉ በክልሉ የትግራይ ቤንሻንጉልና ሌሎች ህዝቦችም ይገኛሉ፡፡

በአዲሲቱ ኢትዮጵያ የአማራ ክልል ህዝቦች ክሌሎች የአገሪቱ ህዝቦች እኩል ተሳትፎና ተጠቃሚነት እንዲኖረው ተደኅል፡፡

በአዲሲቷ ኢትዮጺያ የህዝቦች እኩል ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት እየተረጋገጠ የሚገኘው ከሁሉም በፊት ህዝቦች ብሔራዊ ክልላቸውን ራሳቸው ማስተዳደር መቻላቸውና በፌደራል ደረጃም በእኩልነት መሣተፋቸው ነው፡፡አዲሱ የፓለቲካ ኢኮኖሚ ስርዓት ክልሎችን የማልማት ጉዳይ ከማንም በላይ የራሱ የክልሉ ህዝቦች እንደሆነ በማወቅ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡

ማንኛውም ክልሉ የራሱ ህዝብ ጉልበትና መሬት አቀናጅቶ ከተረባረበ ፤ በክልሉ ያለው የምሁር አቅም የህዝቡን ጥረት ለማገዝ በቁርጠኝነት በመሠለፍ የሚጠበቅበትን ሚና ከተጫወተ የህራዊ ክልሉ የልመልማትና የመለወጥ እድል ዕውን ይሆናል፡፡

በብሄረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን ) የሚመራው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከዚህ መሠረታዊ ግንዛቤ በመነሳት በክልሉ ህዝቦች፤ በባለሀብቶችና በፌደራል መንግስት የተቀናጀ ጥረቶች ክልሉን ማልማት ጀምሯል፡፡

የብሄራዊ ክልሉ ህዝቦች የድህነት ቅነሳ ስራ ዘላቂ በሆነና በማይቆራረጥ ምርትና ምርታማነት ጭማሬ ላይ ስኬታማ የሚባል ውጤት በማስመዝገብ ላይ እንገኛለን፡፡ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን የመጀመሪያው አምስት አመት ዝቅተኛ የእድገት ምጣኔ 11% ከፍተኛው 14% በአማካይ 10.05 % የዕድገት ምጣኔ በማስመዝገብ አንፀባራቂ ስራ ተሰርቷል፡፡

ይህ የዕድገት ምጣኔ ከሌሎች ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ጥቅል ተሳትፎና ልማት ጋር ተዳምሮ በአለማቀፍ ደረጃ ኢትዮጺያ በዕድገት ጎዳና ቀድማ የምትራመድ አገር አድርኅታል፡፡ ይህ ምስክርነት በመሪ ድርጅትና በመንግስት ብቻ የሚሰበክ ዲስኩር ሳይሆን አለማቀፍ እውነታ ሆኖ በአለም ባንክ፤ አለማቀፍ የገንዘብ ፈንድና ሌሎችም ገለልተኛ የሚዲያ አውታሮችና የምጣኔ ሀብት ምሁራን የተናኘ የአዲሱ ሚለኒየም ዜና ነው፡፡

በዚህ ታሪካዊና ታላቅ ዕውነታ ላይ ቆመን ስንናገርና ስናዳምጥ እንደ ሀገር ደስተኞች ብንሆንም አሁን ባልተረጋጋና ትክክለኛ አቅጣጫው ባልተለየበት ዓለማዊ የሽግግር ወቅት እያስመዘገብነው ያለነው ለውጥ የሚያዘናጋ አይደለም፡፡

የአማራ ክልል ህዝቦች በአታጋይ ድርጅታቸው ኢህዴን /ብአዴን መሪነት ፊውዳላዊና አምባገነኑ ስርዓት ዳርጓቸው ከነበረው የልመናና ተመፅዋችነት ክርታሳቸውን ጥለው የራሳቸውን የውስጥ ችግር በራሳቸው የሚፈቱበት ስነ-ልቦና ያደላደለበት ብቻ ሳይሆን በተግባር እያረጋገጡ ይገኛል፡፡

ያለፉት አመታት ተከታታይ ፣ ሁሉን አቀፍና ህብረተሰቡን በየደረጃው ተጠቃሚ የሚያደርገው አንፀባራቂ የኢኮኖሚ ልማት የአማራ ክልል ህዝብ መሪ ድርጅት (ብአዴን) ፣የመንግስትና የመላ ህብረተሰቡ ውጤት ነው፡፡ ይህ ፈጣን ልማት ከጫካ የተሸመጠጠ እንጆሪ እንዳልሆነ ይልቁንም የልማታዊ ፖለቲካል ኢኮኖሚ ሀይሎች፣ ከኪራይ ሰብሳቢ ፖለቲካል ኢኮኖሚ፣ ከአድርባይ ሀይሎች፣ ከፀ-ዲሞክራት ሀይሎች ጋር በተደረገ የሞት ሽረት ትንቅንቅና ይህን የጥገኛ ሀይል በመድፈቅ የተመዘገበ ታሪካዊ ድል ነው፡፡

ከአድርባይና ኪራይ ሰብሳቢ ሀይል ጋር ለመፋለም ራሳቸውን መስዋዕት ባደረጉና አሁንም ሆነ ለወደፊት ለመስዋዕትነት ባዘጋጁ ግንባር ቀደም የልማታዊ ሀይል አባላት ጥረት የተገኘ ድል ነው፡፡ የአማራ ክልል ህዝቦች ሲጠቀሙ ፣ የአማራ ክልል ህዝቦች ሲያልፍላቸው እኔም ያልፍልኛል ፣ ብሎ በሚያምን ግንባር ቀደም ሀይል የተመዘገበ ነው፡፡

ትምክህትንና ጥገኛ አመለካከትን ጊዜና ቦታ ሳይመርጥ በሚታገል ግንባር ቀደም ፣ነፍስና ስጋውን ለህዝብ ጥቅምና ለሀገር ልዕልና ሳያመነታ ተቆራርጦ በሚታገል የብአዴን አመራርና የአማራ ክልል ህዝቦች የተመዘገበ ውጤት ነው፡፡

ሲሳይ መንግስቴ አዲሱ ሰሞኑን ብአዴን የአማራን ክልል ህዝቦች ፣ህወሀት ደግሞ የትግራይ ክልልን ህዝቦች አይወክሉም በሚል አይጋ ፎረም ላይ በፃፉት መጣጥፍ ቁንፅል ሀሳቦችን ብቻ ይዘው ከተሳሳተ ማደማደሚያ ደርሰዋል፡፡ ህወሀትን በተመለከተ አቶ መታሰቢያ ለሲሳይ በፃፉላቸው የመልስ ፅሁፍ ላይ በማያዳግም መንገድ ገልፀውታል፡፡

አቶ ሲሳይ በርዕሰ ጉዳይ ደረጃ ብአዴን/ በስም በተግባርም የአማራን ህዝብ በትክክል አይወክልም የሚመስል ሀሳብ ያራምዱና ወደ መሀል ደግሞ የኢህዴን ወደ ብአዴን መቀየር ጉዳይ ለ23 አመት አባላት የሚያነሱት ጥያቄ ነው፡፡ መቀየር አልነበረበትም የሚል መከራከሪያ የሚመስል ሀሳብ ይሰነዝራሉ፡፡

ስምና ስያሜን በተመለከተ አቶ ሲሳይ እንደ ጥሩ ማሳያ አድርገው የጠቀሱት ደግሞ ብአዴን/ኢህዴንን ሳይሆን ኦነግን ፤ ኢህአፓን፤ መኢሶንን ወዘተ.... የጥሩ ፖለቲካ ፓርቲ ስም አወጣጥ ማሳያ አድርገው ማቅረባቸው የአቶ ሲሳይን ዝንባሌ በግልፅ የሚያሳይ ይመስለኛል፡፡

ለማነኛውም ኢህአፓ ለትግል የሚሆን አስቻይ ሁኔታ በነበረበት ወቅት ታጋዩንና ትግሉን በትኖ ከሄደ በኋላ አምባገነናዊ ስርዓቱን ለመፋለምና የትግሉን ቀጣይነት ለማረጋገጥ ከልዩ ልዩ የአገሪቱ ክፍል የተወጣቱ ወጣቶች በኢህዴን ስር ተሰባሰቡ፡፡

የማታ ማታም ደርግ ግብዓተ መሬት መግባቱ መቃረቡ ሲታወቅ በኢህዴን ውስጥ የነበሩ የተለያየ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ጓዶች ወደ የብሄራዊ ድርጅቶቻቸው ተቀላቀሉ፡፡ ብአዴን የአማራ ክክል ውስጥ ከሚገኙ ልዩ ልዩ ብሄሮችና ብሄረሰቦች የተውጣጡ ጓችን ይዞ የአማራ ህዝብች የንቅናቄ ድርጅት ሆኖ ተመሰረተ፡፡ ታዲያ ይህ ታሪክ ምን እንከን ይወጣለታል፡፡

የብሄረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ ኢህዴን /ብአዴን በኢትዮጲያ ለፍትህና ዴሞክራሲ መስፈን የአማራንና በአማራ ብሄራዊ ክልል ውስጥ የሚገኙ ብሄረሰቦች ህዝቦችን ከጎኑ አሰልፎ ያለማለሳለስ እንደታገለ ሁሉ ዛሬም የአገር አቀፉ አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ሀይል አካል በመሆን ለአብዮታዊ ዲሞክራሲ ፕሮግራም በአንድ በኩል በሰፌው የአማራ ክልል ህዝቦች ወሳኝ ተሳትፎ በብሄራዊ ክልሉ ደረጃ ተፈፃሚ ለማድረግ በሌላ በኩል ደግሞ ፕሮግራሙ በአገር አቀፍ ደረጃ ተፈፃሚ እንዲሆን የበኩሉን አስተዋፅኦ በማድረግ ላይ የሚገኝ አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት ነው፡፡

ታዲያ ከዚህ ውጭ የህዝብ ውክልና በምን ይገለፃል? ህዝብንና ብሄራዊ ክልልን በፈጣን ልማት ከማሳተፍና ተጠቃሚ ከማድረግ ፤በየጊዜው እያደገ በሚሄድ የመልካም አስተዳደርና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ውጭ ውክልና ወይም የህዝብ እንደራሴነት መለኪያው ምንድን ነው ?

ብአዴን የአማራ ክልል ህዝቦች መሪ ድርጅት ነው ስንል፤ በሺ የሚቆጠሩ ታጋዮች የአካልና የህይወት መስዋዕትነት የከፈሉበት ድርጅት ማለታችን ነው፡፡ ይህን ታላቅና ግዙፍ እውነታ ከግል ፍላጎት በሚመነጭ ምክንት ማጠልሸት ተገቢ አይደለም ፡፡ በውስጡ እየኖርን ያልሆነልንን እና ጥቂቶች ቆራቶች እየተሰው ሀገርና ህዝብ ለመቀየር እየተጉ ባሉበት ሁኔታ ትግልን ለማኮላሸትና የክልልን ህዝቦች አንድነት ለመናድ

የሚሞክር ጥያቄ ማንሳትና ማጣጣል የህዝብ ወገንተኝነት ሊሆን አይችልም፡፡ ለምሁራዊ መራቀቅና ፍልስፍና ሲባል ሊነሳ የሚችል ጥያቄና አስተያየትም ሊሆን አይችልም ፡፡

የህዝብ ውክልና ማለት ምን ማለት ነው? የአማራ ህዝብ ራሱን በራሱ እያስተዳደረ አይደለም ነው? ወይስ የአገው-አዊና የአገው ህምጣ ብሄረሰብ ወይም ኦሮሞዎች በራሳቸው ቋንቋ አይማሩም ? የራሳቸውን መልካዓ ምድር እንዳያለሙ ተነጥቀዋል ወይስ ራሳቸው በመረጧቸው መሪዎች አይዳኙምና አይመሩም ለማለት ነው ? የብሄራዊ ክልሉ መንግስት ከፍተኛ የስልጣን አካል በሆነው በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ውክልና የላቸውም ማለት ተፈልጎ ይሆን አቶ ሲሳይ ከትንተናቸው በላይ የደረሱበት ማደማደሚያ ስህተት ላይ ጥሏቸዋል፡፡

ቸር እንሰንብት!!!